# መመሪያ ቁጥር 225/2013

## ወደ ውጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጎማ መመሪያ

በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን የ11 በመቶ አማካይ አመታዊ የኢኮኖሚ እድገት ግብ ለማሳካት በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ከአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ ኤክስፖርት የሚገኘውን አመታዊ ገቢ ከ201.7 ሚሊዮን ወደ 1,483 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማሳደግ የታቀደ በመሆኑ፣

በአዲስ ማስጦር ይህንን የሆልቲካልቸር ልማት ግብ ለማሳካት የገበያ፣ የሎጂስቲክና የትራንስፖርት ችግሮችን በመፍታት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ ምርት ወጠዎችን ከመቀሌና ባህር ዳር የማጓጓዣ ወጪ ከአዲስ አበባ የኤክስፖርት ማጓጓዣ ወጪ ጋር የሚመጣጠን ያለመሆኑ በሁለቱ ክልሎች አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ አምርተው ወደ ወጪ የሚልኩ ባለሀብቶች በወጪ ገበያ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖ የፈጠረ በመሆኑ፣

ይህንን ችግር በሚቃለል በሁለቱ ክልሎች በሆርቲካልቸር ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶችን ለመደገፍ በአዲስ አበባ እና በሁለቱ ክልሎች መካከል የሚታየውን የሆርቲካልቸር ምርቶች የአየር ትራንስፖርት ታሪፍ ልዩነት በመደጎም የትራንስፖርት ወጪውን ተመሳሳይ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ወደ ውጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ መመሪያ ቁጥር 225/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ የሆርቲካልቸር ምርቶች ማለት የአበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ ምርቶች ማለት ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ የሆርቲካልቸር ምርቶችን ከመቀሌና ከባህር ዳር ኤርፖርቶች ለማጓጓዝ የሚጠየቀውን የትራንስፖርት ታሪፍ ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ማጓጓዣ ታሪፍ

ጋር ተመሳሳይ ለማድረግ በሦስቱ የበረራ ማስመሮች መካከል የሚታየውን የታሪፍ ልዩነት በመንግስትና በኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲሸፈን በማድረግ ኤክስፖርቱን መደገፍ ነው፡፡

## 4. <u>የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረግ የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ ተጠቃሚ የሚሆኑት በባህር ዳርና መቀሌ አካባቢዎች በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ተሰማርተው ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ የሚልኩ ድርጅቶች ብቻ ናቸው፡፡

## 5. <u>የትራንስፖርት ወጪ ማጋራት</u>

1. የሆርቲካልቸር ምርቶችን ከመቀሌና ባህር ዳር ኤርፖርቶች የማጓጓዣ ሂሣብ ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ማጓጓዣ የአየር ትራንስፖርት ሂሣብ ጋር ተመሳሳይ ለማድረግ ከሚታየው የዋጋ ልዩነት 2/3ኛው በመንግስት 1/3ኛው በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

2. ከባህርዳር ወደአዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት የሚጓጓዘውን የአበባ ምርት ማጓጓዣ ወጪ ሙሉ በሙሉ መንግስት ይሸፍናል፡፡

## 6. <u>ከዚህ መመሪያ አፈፃፀም ጋር ግንኙነት ያላቸው ተቋሞች የሥራ ድርሻ</u>

### 6.1. <u>የሆርቲካልቸር አምራቶች</u>

ሀ. በኢትዮጵያ አየር መንገድ በሚያዘላቸው የበረራ ፕሮግራም መሠረት ማሟላት የሚገባቸውን ፎርማሊቲዎች/ ሰነዶች አዘጋጅተው ምርቶቻቸውን ለጭነት ማቅረብ አለባቸው፡፡

ለ. በአወሮፕላን ተጓጉዞ ወደ ውጭ ለተላከው ምርት ብቻ የድጎማ ክፍያ ይጠይቃሉ፡፡ ለዚህም ተገቢውን ሰነድ ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ያቀርባሉ፡፡

ሐ. አበባ አምርተው ወደ ውጭ ለመላክ ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት የሚያጓጉዙ ድርጅቶች ደግሞ ለማጓጓዣ ያወጡትን ወጪ የሚያረጋግጥ ሰነድ ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

## 6.2. የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ

ሀ. በዚህ መመሪያ መሠረት ለየሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች ለሚደረገው የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የሚውል የበጀት ጥያቄ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

ለ. ወደውጭ የተላከውን የሆርቲካልቸር ምርት ማጠን፣ በላኪዎች በማለየት የሰነድ መረጃዎች ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እንዲሁም ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ አበባ አምራቾች አሰባስቦ ይይዛል፡፡ የሰነዱንም ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

ሐ. ባሰባሰበው መረጃ መሠረት የሚያስፈልገውን የድጎማ ገንዘብ እንዲለቀቅለት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በጽሑፍ ጥያቄ ያቀርባል፡፡

መ. የጠየቀው የድጎማ ገንዘብ ሲለቀቅለት የሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች ለወጪ ገበያ በላኩት ምርት ማጠን ገንዘቡን ይከፍላል፡፡ ለዚህም ተገቢውን የሂሣብ ሰነድ ይይዛል፡፡ የክፍያ አፈፃፀም ሪፖርትም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየወሩ ያቀርባል፡፡

## 6.3. የኢትዮጵያ አየር መንገድ

ሀ. የሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች በያዘው የበረራ ፕሮግራም መሠረት በቂ የጭነት አወሮፕላን ያቀርባል፡፡

ለ. ወደውጭ ያጓጓዘውን የሆርቲካልቸር ምርቶች ማጠን እንዲሁም የላኪ ድርጅቶችን ስም የያዘ መረጃ ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ይሰጣል፣ የአፈፃፀም ሪፖርትም በየወሩ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

## 6.4. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የሆርቲካልቸር ምርቶች አምራቾች ወደ ውጭ የላኩትን የምርት አይነትና ማጠን በየድርጅቶቹ በማለየት ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ያቀርባል፡፡

### 6.5. የትራንስፖርት ሚኒስቴር

በመመሪያው አፈፃፀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ደጋፍ ያደርጋል፡፡

### 6.6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

ሀ. ከኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ለሆርቲካልቸር ምርቶች የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የሚውል በጀት ይይዛል፡፡

ለ. የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የድጎማ ገንዘብ እንዲለቀቅለት በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ገንዘቡን ወደ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ የባንክ ሂሣብ ያስተላልፋል፡፡

ሐ. የተለቀቀውን ገንዘብ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የራሱን ኢንስፔክተሮች በድን በማሰማራት የሂሣብ ምርመራ ያደርጋል፡፡ ስህተት ከተፈፀመም ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል/ያስወስዳል፡፡

## 7. የድጎማ ክፍያ የቆይታ ጊዜ

በዚህ መመሪያ መሠረት ለሆርቲካልቸር ምርቶች ኤክስፖርት የትራንስፖርት ወጪ ድጎማ የሚደረገው ለ2006 የበጀት አመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ይህ ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል፡፡

## 8. መመሪያው በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

*አዲስ አበባ ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ሚኒስትር*